# ▪ በቪክቶሪያ AMIEU ቅርንጫፍ እንኳን ደህና መጡ

ወደ የስጋ ሥራ እንኳን ደህና መጡ፤ እንዲሁም በአወስትራሊያ ወስጥ ሥራ በማግኘቱ እንኳን ደስ ያለዎት። እርስዎ የህብረቱ አባል የሆኑ ዘንድ እድሉን ለማቅረብ እፈልጋለሁ። ይህም በአወስትራሊያ ወስጥ በስጋ ፋብሪካ ለሚሰሩ ያካተተ ይሆናል።

በኢትዮጵያ ወስጥ የሚኖ ህብረት ከአወስትራሊያ ካሉት ማህበራት ፍጹም የተለየ መሆኑን ስለማወቅ ታዲያ የስጋ ማህበር (AMIEU) እንዴት እንደሚሰራ ለማብራራት እፈልጋለሁ።

**በአወስትራሊያ ወስጥ ብዙዎቹ የስጋ አሰራር ሂደት ሰራተኞች የAMIEU አባላትና ተሳታፊ ይሆናሉ፤ ምክንያቱም ማህበሩ እነሱን በመወከል ጠቃሚ የሆነ ሚና ስለሚጫወት ነው።** በአወስትራሊያ ወስጥ የማህበር አባል መሆን ግዴታ አይደለም እንዲሁም አባል እንዲሆኑ ማደድ የለብዎትም። በተጨማሪም ቀጣሪዎች የማህበሩ አባል ለሆነ ማንኛወም ሰው ላይ አድልዎ መፍጠር አይችሉም።

በማህበራችን አባል ለመሆን በነጻ ሲሆን ታዲያ አባል በመሆንዎ ቀጣሪዎ በርስዎ ላይ አድልዎ ወይም ጭቅቀት መፍጠር አይችልም። Swift ብዙ የማህበር አባላት ሲኖሩት ታዲያ የማህበር አባል በመሆናቸው ለአንዳቸወም ያለ አግባብ አቀባበል ተደርጎባቸው አያወቅም።

## ማህበርዎ እንዴት እንደሚሰራ

ከ100 ዓመታት ጊዜ በላይ የሚቆጠር AMIEU የሚያኮራ ታሪክ አለው። በአጠቃላይ እኛ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ስንሆን ኃላፊዎቻችን በሙሉ በየአራት ዓመቱ ይመረጣሉ። በሥራ ቦታዎ ላይ የተመረጡ ተወካዮች ያገኛሉ። እነዚህ ሰዎች በአካባቢዎ የሚገኙ ሲሆኑ እርስዎን ለመርዳት በጣም ደስተኛ ሲሆኑ ብቻ ነው።

እንዲሁም በማህበርዎ ለብዙ ጉዳዮች፣ ድርድሮችና ክርክሮችን የሚቆጣጠር የሙሉ−ቀን አዘጋጅ ሠራተኛ ይኖራል። የርስዎ አቀናጅ በ Swift, Graham Bird or Jim Brittain ይባላል። .

## ማህበርዎ የርስዎ ደመወዝና ሁኔታዎች እንዲሻሻልና እንዲጠበቅ ያደርጋል።

በስጋ ፋብሪካ ወስጥ መሥራት ከባድና ተደጋጋሚ ቢሆንም ነገር ግን ጥሩ ደመወዝና ጥሩ ሁኔታዎችን ያገኛሉ። ታዲያ እነዚህ ጥሩ ሁኔታዎች ሊገኙ የሚችሉት ሠራተኞች በማህበሩ አባላት ከሆኑና ለተሻለ የኑሮ ደረጃ በጣምራ ሲከራከሩ ብቻ ነው። በ Swift በኩል ጥሩ ደመወዝና የሚከተሉትን ሁኔታዎች ያገኛሉ:

**ለእረፍት ሲወጡ የአራት ሳምንታት ክፍያ**

ምንም እንኳን ቀደም ብለው ለእረፍት ባይወጡም ከኩባንያው ሥራ ሲያቆሙ የእረፍት ጊዜው ክፍያ ይሰጥዎታ። እንዲሁም ከእረፍት ክፍያዎ በተጨማሪ 17.5% ሊከፈል ይችሉ ይሆናል። ስለ የእረፍት ተጨማሪ ክፍያ መብትዎ በተመለከተ የአካባቢዎን ተወካይ ወይም አዘጋጅ ሠራተኛ ይጠይቁ።

**ለህመም ፈቃድ ክፍያ**

በዓመት እስከ 10 ቀናት የሚሆን የህመም ፈቃድ ያገኛሉ፣ ይሁን እንጂ የህመም ፈቃዱን ካልወሰዱ ከኩባንያው ሥራ ሲያቆሙ ወይም ለገና በዓል የዓመት ፈቃድ ሲወጡ ላልተጠቀሙበት የህመም ፈቃድ ይከፈልዎታል።

**ከስራ ሰአት በላይ Overtime**

ካለዎ የመደበኛ ቀናት በላይ የሚሰሩ ከሆነ ለሠሩበት ተጨማሪ ጊዜ በከፍተኛ ተመን ይከፈልዎታል።

**ለጡረታ/Superannuation**

ከመደበኛ ክፍያዎ 9% የሚሆን ተጨማሪ ገንዘብ በስምዎ በጡረታ አካወንት ወስጥ ይገባልዎታል።
በቪክቶሪያ ቅርንጫፍ በተቋቋመ AMIEU ለስጋ ኢንዱስትሪ ተቀጣሪዎች የጡረታ ገንዘብ (MIESF) በኩል የርስዎ ጡረታ ይከፈላል።

**ለጤና ጥበቃና ደህንነት አያያዝ**

የጤናና ድህንነት ተወካዮች፣ የድጋፍ ሰጭ ኃላፊና የማህበሩ ጤናና ድህንነት አቀናጅ በሆኑት Gwynnyth Evans የርስዎ ሥራ ቦታ ድህንነት የተጠበቀና አደጋ እንዳይደርስ በመከላከል ይረዳል።

**ዎርክ ከቨር/WorkCover**
በሥራ ላይ ከተጎዱ Gwynnyth Evans ምክር በማቅረብ እርስዎን በመወከል ይረዳዎታል። የህግ ጠበቃ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሊረዳዎ ወደሚችል የህግ ባለሙያ ይልክዎታል።

እነዚህ በሥራ ቦታዎ ላይ ከሚቀርቡት ወስጥ ማጠነኛ ሁኔታዎች ምሳሌዎች ናቸው። ብዛት ባለው የስጋ ሥራዎች ላይ ደመወዝና ሁኔታዎች በንግድ ድርጅቱ ስምምነት ማሰረት ሲተዳደር ይህም በሠራተኞችና በራሳቸው AMIEU ማህበር አማካኝነት ድርድር ይደረጋል።

**ይህ እውነት ነው** – በማህበር ስምምነት ካደረጉ ሠራተኞች ጋር ሲማዛዘን በማህበር ስምምነት ያልታቀፉ የአወስትራሊያ ሠራተኞች **ዝቅተኛ** የደመወዝ ጭማሪ ያገኛሉ። ለዚህ ነው በማህበሩ አባል መሆን ጠቃሚ የሆነ ው።

## <u>አባል በመሆን ሌሎች ጥቅሞች</u>

- በማንኛወም የኢንዱስትሪ ጉዳይን በተማለከተ ከቀጣሪው ጋር ሲደራደሩ ወክልና ማሰጠት።
- ለሠራተኞች ድህንነቱ የተጠበቀ የሥራ ቦታ እንዲኖር ማርዳት።
- የሠራተኛን ካሳ ጉዳይ በተማለከተ ምክርና ወክልና ማቅረብ።
- ብዙጊዜ የሚወጣ ጋዜጣና የማህበሩ መፅሄት – "ለስጋ ሠራተኞች" ማሰጠት።
- የህጋዊ የሆነ አገልግሎትን ማልገያና በነጻ ህጋዊ የሆነ ምክር እንዲያገኙ ማድረግ።
- ብዛት ያለወና የተለያዩ እቃዎችና አገልግሎቶችን በሚዛዙበት ጊዜ "በማህበሩ ገብያተኛ" በኩል ታላቅ የቅናሽ ዋጋ ማግኘትና ገንዘብ ማትረፍ ይሆናል።

## <u>አድልዎ መፍጠርና ማስጨነቅ</u>

አባላቶቻችን በሥራ ቦታ ላይ እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው የሚገልጽ በጣም ጥብቅ የሆነ ፖሊሲ AMIEU ማህበር ይኖረዋል። በተቆጣጣሪዎችና በረዳት ሠራተኞች በኩል ለሁሉም ሠራተኛ በአግባብ የማስተንግዶ መብት ይጠበቃል ብለን እናምናለን። ብስጭት ወይም አድልዎ ለደረሰበት ማንኛወም አባላቶቻችን ማስጠራዊ በሆነ መሜክርት በማቅረብና ከአስተዳደር ጋር ያለው መብታቸው ይጠበቅ ዘንድ በፀረ–አድልዎ ኮሚሽን ፊት በቀርበን እንረዳለን።

## <u>ለማህበሩ የሚከፈለው በየሳምንቱና ግብር/ታክስ ተቆራጭ ይሆናል</u>

AMIEU የደመወዝ መቁረጫ ቅጽ ከተጠናቀቀ በኋላ ለርስዎ ማህበር የሚከፈለው ከደመወዝዎ በየሳምንቱ ተቆራጭ ይሆናል። ክፍያው በሳምንት $7.70 ዶላር ሲሆን ከሳምንታዊ ደመወዝዎ ከ1% በታች ያነሰ ነ ው።

በየሳምንቱ ከሚያገኙት ደመወዝ ላይ የገቢ ግብር/ታክስ በአወስትራሊያ መንግሥት ሲቀንስ ያወቁታ። በአወስትራሊያ ያለው አሰራር በየሳምንቱ ከሚያገኙት ደመወዝ መንግሥት የገቢ ግብር/ታክስ ይቆርጣል፤ ታዲያ የተወሰነወን ገንዘብ በፋይናንስ ሜጨሻ ዓመት ላይ እንዲማለስልዎ ማጠየቅ ይችላሉ።

በአንዳንድ እቃዎች ላይ ባወጡት ገንዘብ ብቻ ላይ እንዲማለስልዎ ማጠየቅ ይችላሉ። እነዚህ ዝርዝር እቃዎች ታክስ የሚቆረጥባቸው ዝርዝሮች ተብለው ይጠራሉ፣ እንዲሁም ለርስዎ ማህበር ሳምንታዊ ክፍያም ከነዚህ ዝርዝሮች አንዱ ይሆናል። ስለዚህ ለማህበርዎ የከፈሉትን በታክስ በኩል ተማላሽ እንዲሆን ማማልከት ይችላሉ ካልሆነም ርካሽ እንደሆነ ነ ው።

ከሥራ ባልደረቦችዎ ጋር አብረው በማተፍ የማህበራችን አባል ይሆኑ ዘንድ በጥብቅ አሳስባለሁ። ማሉ የAMIEU አባል ለመሆን እባክዎ ከደመወዝ የመቁረጫ ስምምነት ቅጹ ያጠናቅቁ። በአወስትራሊያ ቆይታዎ የደስታና ሀብታም ያደርግልዎ እማኛለሁ።

**GRAHAM BIRD**
**የቪክቶሪያ ቅርንጫፍ ፀሐፊ/VICTORIAN BRANCH SECRETARY**
**AMIEU**
**ግንቦት/May 2008**